# 26 የፖለቲካ ስደተኞች ሱዳን ውስጥ የት እንደታሰሩ ታወቀ ! በግድ ወደ ኢትዮጵያ ማባረሩም ለጊዜው ተገታ !

ገረመው ሃይሉ
ህምሌ 29ቀን 1999ዓ.ም

እንደሚታወቀው የሱዳን መንግስት የጸጥታ ሃይሎች ህምሌ መጀመሪያ ላይ ጀምሮ ለብዙ ቀናት በዘለቀ አሰሳ በአንድ በኩል በትጥቅ የወያኔን መንግስት ከሚታገሉ ሃይሎች ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ የጠረጠራቸውን ከ24 በላይ የፖለቲካ ስደተኞችን በሌላ በኩል ደግሞ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ህጋዊ የመኖሪያ ፈቃዳ የሌላቸውን ኢትዮጵያውን ማሰሩን መገለጹ ይታወሳል።

ህጋዊ መታወቂያ ባለመኖራቸውና የሱዳንን ባህል ይበርዛሉ በሚል የተያዙትን አብዛኞችን ኢትዮጵያውያን የሱዳን መንግስት ለፍርድ ቤት አቅርቦ የገንዘብና ከ5-30 በሚደርሱ ቀናት እስራት ከቀጣ በኋላ ወደ አገር እንዲመለሱ መፍረድ ጀምሮ ነበር። ይሁንና በህገር ወዳዶችና በሰብባዊ መብት ተከራካሪዎች አማካይነት ከውጭም ከውስጥም በተደረገው ከፍተኛ ርብርቦሽና ጨና ወደ አገር በግድ መመለሱ ሊገታ ችሏል። አብዛኞቹም በዋስ ሊፈቱ ችለዋል። የተቀሩትም እንደሚፈቱ ተስፋ አለ።

አሳሳቢ ሆኖ የቆውና አሁንም አሳሳቢ የሆነው መዳረሻቸው ጠፍቶ የነበረው የፖለቲካ ስደተኞቹ ጉዳይ ነው። ህምሌ ቅዳሜ 28ቀን 1999 ዓ.ም በተገኘው ዜና መሰረት 26ቱ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ስደተኞች ደበቅ በተባለ በእንግሊዞች የቅኝ አገዛዝ ዘመን በተሰራ የወንጀለኞች እስርቤት ታስረው እንደሚገኙ ታውቋል። ከካርቱም ወጣ ብሎ ከሚገኘው ከ ደበቅ እስርቤት በህመም ምክንያት ከተፈቱ ሁለት ኢትዮጵያውን በተገኘው መረጃ መሰረት ከወራት በፊት የት እንደገባ ጠፍቶ የነበረው አቶ አቸነፈ እና ከገዳሪፍ የተያዙት ሽማግሌው አጣናው ዋሴ በዚሁ እስርቤት ውስጥ እንደሚገኙ ታወቋል። በህመም ከተፈቱት ኢትዮያውያን ውስጥ አንዱ የኦነግ ደጋፊ የኦሮሞ ተወላጅ ሲሆን ሁለተኛው በአርበኞች ግንባር አባልነት የተከሰሰ ነው። ከሁለት ወራት በፊት ከእምራኩባ የስደተኞች ጣቢያ ከተያዘ በኋላ የት እንደገባ ያልታወቀው ቀናው ድልነሳ የተባለ የአርበኞች ግንባር አባል በዚህ እስርቤት ውስጥ አለመኖር የሱዳን መንግስት ለወያኔ አሳልፎ ሰጥቶታል የሚለውን ጥርጣሬ አጠናክሮታል። ኢትዮጵያውያኑ የፖለቲካ ስደተኞች እንደተያዙ የተጠየቁት በ ኤርትራ መንግስት ከሚደገፉ ታጣቂ ድርጅቶች ጋር ግንኙት እንደሚያደርጉና እንደማያደርጉ መሆኑ ታውቋል። እነዚህን የፖለቲካ ስደተኞች የሱዳን መንግስት በወያኔ ጠያቂነት መሰረት የወያኔ ሚሊኒየም እስከሚያልፍ ድረስ እስርቤት ያቆያቸዋል የሚል ከፍተኛ ጥርጣሬ አለ።